ትሠማኝ ይሆን? ዛሬም እንደ ትናንቱ

አዲወሰኔ ዶለኪያ

ብራዋስያ ሃዋዛ

ጨው በር ሣንቃ በር

አምባራስ ባርና

ደረሰጌ ጃናሞራ

እራስ ዳሸን  ወጥቼ

አቤ ደብተራው  አቤ ደብተራው

እያልኩኝ ብጣራ

ትሰማኝ ይሆን? ዛሬም እንደትናንቱ

መና መቀጥዋ እብናት

ዳሁጭ ሰንኪ

ሃሙሲት ጉሃላ

አርባያ ወራህላ

በለሳ ወርጄ

አቤ ደብተራው

ሞረሽ ብዬ ብጣራ

ትሰማኝ ይሆን? ዛሬም እንደትናንቱ

ከናባስበር መንደር

ወልቃይት ጠገዴ

አጅሬ ጃኖራ

ከተራራው ወጥቼ

አቤ ደብተራው

ሞረሽ እያልኩ ብጣራ

ትሰማኝ ይሆን?ዛሬም እንደትናንቱ

ወርቅምድር ገምበራ

ጠባሪ ፈልፈል ዓርማጭሆ

እማነኮይት  ዳዛ

ካፋፉ ቁሜ

አቤ ደብተራው  ሞረሽ

ብየ ብጣራ

ትሰማኝ ይሆን?ዛሬም እንደትናንቱ

ነጋዴ ብህር ደንገል

ቦህቦህ ዋኒ

አለፋ ጣቁሳ

ሰራቆ ዘገርጌ

አንተም ወንድ ላይ ቁሜ

ሞረሽ አቤ ደብተራው

እያልኩ ብጣራ

ትሰማኘ ይሆ? ዛሬም እንደትናንቱ

አሞራ ኪቢን ወጥቼ

ቋራ ወሚደላ

ዎፍታ ገብስ ገቢያ

ቴዎድሮስ ከተማ ቁሜ

አቤ ደብተራው

ሞረሽ እያልኩ ብጣራ

ትሰማኝ ይሆን? ዛሬም እንደትናንቱ

አቤ ላብአደሩ አቤ አርሶአደሩ

አቤ ወታደሩ  አቤ ኮሚሳሩ

አቤ ተማሪው አቤ አስተማሪው

አቤ ደብተራው  አያልኩ

ሞረሽ ብዬ ብጣራ

ትሰማኝ ይሆን? ዛሬም እንደትናንቱ

አቤ ደብተራው

የላብአደሩ ክንድ

የአርሶአደሩ ጉልበት

የትግሉን ደልዳላ ትክሻ

አቤ ደብተራው

ለቀኝ አድርባዩ ለግራ አድርባዩ

ላንጃ ለባንዳው

ለዘረኛ ለፋሽስቶች

ለተገንጣይ ለምንደኞች

እሳተ ጎሞራውን

የንሃሴውን መብረቅ

ተሎ እንዲደርስልኝ  ድምጹ እንድሰማው

አቤ ደብተራው ሞረሽ

ሞረሽ አቤ ደብተራው

አንድ ኢትዮጵያ አንድ ኢህአፓ